# ጨብጥ [GONORÈ]

ጨብጥ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን በሽታው በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሳቢያ በፍትወተ-ሥጋ ብልቶች መካከል ወይም በፍትወተ-ሥጋ ብልትና በአፍ ወይም በፍንጥጣ ውስጥ ባለ ስስ ሽፋን [**mucous membrane**] መካከል ንክክ ሲኖር ነው። በሽታው በጣም ተላላፊ የሆነና የመተላለፉም ምክንያት ጎኖኮከን የተባለ ባክቴሪያ ነው። ጎኖኮከን በስስ ሽፋኖች ውስጥ መኖር የሚስማማውና በአብዛኛው ብልቶች፤ በሽንት ቱቦ፤ በፍንጥጣና በሰርቭክስ ውስጥ ይገኛል። ባክተሪያው ወደ ደምና ሌሎች የሰውነት ክፍሎች ሊዛመትና በእነዚህ ውስጥ ሕመም ሊያመጣ ይችላል። ለጊዜው ጨብጥ በኖርዌይ ውስጥ በጣም አልፎ አልፎ ብቻ የሚታይ በሽታ ነው። በሌላ የዓለም ክፍል ግን በሽታው በጣም ተዛምቶአል።

ኮንደምን መጠቀም በበሽታው ከመያዝ ይከላከላል። የግብረ-ሥጋ ግንኙነቱ እስክፈጸም ድረስ ኮንዶሙ መውጣት የለበትም።

## ምልክቶች [Symptomer]

ለብዙዎቹ ወንዶች በጨብጥ የመያዝ ምልክት ከአንድ እስከ ሁለት ቀኖች በኋላ ወይም በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ይታያል። ሽንት ስሸናም የሚያቃጠል/የሚጠዘጥዝ ሕመም ይኖራል። በአብዛኛው ወፍራም የሆነ ፈሳሽም ከሽንት ቱቦ ይፈሳል። በወንዶች ላይ ጨብጥ ወደ የወንድ የዘር-ፍሬ በመዛመት እንዲመክኑ ሊያደርግ ይችላል።

ሴቶች የወንዶችን የሚመስል የበሽታው ምልክት ሊያዩ ይችላሉ። በተጨማሪም በፍትወተ-ሥጋ ብልታችው ፍሳሽ ይመጣል። የበሽታ ምልክቶቹ ከወንዶች አንፃር ደካማዎች ናቸው። በጣም አንስተኛ በመሆናቸውም የተነሳ ብዙውን ጊዜ በበሽታው መያዝን ማወቅ አይቻልም። ሴቶች በተጨማሪም አልፎ አልፎ ደም ሊፈሳቸው ይችላል። ጨብጡ በሴቶች የዕንቁላል ቱቦ ሊዛመትና ሊያመክናቸው ይችላል።

አንዲት ሴት በወሊድ ጊዜ ጨብጥ ካለባት የተወለደው ሕፃን የዓይን ሕመም ሊያጋጥመው ይችላል። ጨብጡ ሕክምና ካላገኘ አዲስ የተወለደው ሕፃን በተወሰኑ አጭር ቀኖች ውስጥ ሊታወር ይችላል።

## ምርመራው [Undersøkelse]

የጨብጥ ምርመራ ናሙናዎች በጥጥ በተሸፈነ ቀጭን እንጨት ጫፍ ከሽንት ቱቦና ከማሕፀን አፍ እንደ አስፈላጊነቱም ከማሕፀን አንገትና ከፍንጥጣ ይወሰዳል። ማራባት የሚቻል ናሙና ይወሰድና ወደ ላቦራቶሪ ይላካል።

## ህክምናው [Behandling]

ጨብጥ በአንቲባዮቲክ ይታከማል። መድኃኒቱን የሚወስዱ ሁሉ ከአንድ እስከ ሁለት ሳምንቶች ጊዜ ውስጥ ለክትትል ምርመራ መቅረብ አለባቸው። መድኃኒቱን የሚወስደው ሰው መዳኑን ለማረጋገጥ አዲስ የላቦራቶሪ ናሙናዎች ይወሰዳሉ።

አንድ ሰው ለመዳኑ ለክትትል ምርመራ ቀርቦ ከበሽታው ነፃ መሆኑ ከመረጋገጡ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የለበትም።

## ነፃ ምርመራና ሕክምና [Gratis undersøkelse og behandling]

በተላላፊ በሽታዎች መከላከያ ሕግ መሠረት ጨብጥ ለሕብረተሰቡ ሁሉ አደገኛ ተላላፊ በሽታ ተደርጎ ይተረጎማል። ይህም ማለት ማንም ለነፃ ምርመራና ሕክምና መብት አለው። አንድ ሰው በበሽታው ከተያዘ አሁን ላለው (ላላት) ወይም ቀደሞ ለነበረው (ለነበራት) የፍቅር ጓደኛ ማሳወቅ

በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት አማካይነት በሽታው ወደ ሌላ ሰው መተላለፉን ለማረጋገጥና ለማከም እንዲቻል ሐኪሙና በሽተኛው በመተባበር በሽታው የተዛመተባችውን መስመሮች ይከታተላሉ፡፡